አዋጅ ቁጥር----/2015

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ

# ሠራዊት አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ሠራዊት የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋፅዖ ያካተተና ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነፃ በመሆን ተግባሩን እንዲያከናውን የተደራጀ መሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ሠራዊት የሚመራበትንና ከተ❼ሙ ወቅታዊ ግዳጅ ጋር የሚጣጣም እንዲሁም የወደፊቱን ግዳጅ ታሳቢ ያደረገ የህግ ማዕቀፍ የሚያስፈልገው በመሆኑ፤

በሥራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመከላከያ ሠራዊት የህግ ማዕቀፍ ማሻሻልና ማጠቃለል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር……………. /2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "አዛዥ»" ማለት የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥን ጨምሮ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ላይ የሚገኝ አንድን የጦር ክፍል ለመምራትና ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

2/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

3/ "ምልምል ወታደር" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ በውትድርና ለማገልገል መስፈርቱን አሟልቶ ከህብረተሰቡ ውስጥ የተመለመለ ሆኖ ወታደራዊ ስልጠናውን ያላጠናቀቀና የቅጥር ውል ያልፈረመ ሰው ነው፤

4/ "የሠራዊት አባል" ማለት በየደረጃው የሚያስፈልገውን የውትድርና ስልጠና ወስዶ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ቢያንስ ለ7 ወይም 10 ዓመታት የአገልግሎት ውል ፈርሞ የውትድርና አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሰው ነው፤

5/ "መሠረታዊ ወታደር" ማለት መሠረታዊ የውትድርና ስልጠና አጠናቆ ቃለ መሃላና የቅጥር ውል የፈጸመና የውትድርና አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጀ ወይም በማገልገል ላይ ያለና ማዕረግ ያልለበሰ ወይም ያልተሰጠው የሠራዊት አባል ነው፤

6/ “መኮንን“ ማለት ከምክትል የመቶ አለቃ እስከ ጀነራል ወይም አቻ ወታደራዊ ማዕረግ የለበሰ የሠራዊት አባል ነው፤

7/ “ጀነራል መኮንን“ ማለት ከብርጋዴር ጀነራል እስከ ጀነራል ወይም አቻ ወታደራዊ ማዕረግ የለበሰ የሠራዊት አባል ነው፤

8/ “ፊልድ ማርሻል” አገርን ከከፍተኛ የደህንነት ስጋት ለማውጣት ለሚፈፀም ከፍተኛ የውትድርና አመራር ብቃት በልዩ ሁኔታ በ አገሪቱ ርዕሰ ብሄር የሚሰጥ ከፍተኛው የውትድርና ማዕረግ ነው፤

9/ “ከፍተኛ መኮንን” ማለት ከሻለቃ እስከ ኰሎኔል ወይም አቻ ወታደራዊ ማዕረግ የለበሰ የሠራዊት አባል ነው፤

10/ “መስመራዊ መኮንን” ማለት ከምክትል የመቶ አለቃ እስከ ሻምበል ወይም አቻ ወታደራዊ ማዕረግ የለበሰ የሠራዊት አባል ነው፤

11/ “የበታች ሹም” ማለት ከምክትል አስር ዓለቃ እስከ ቺፍ ዋራንት ኦፊሰር ወይም አቻ ወታደራዊ ማዕረግ የለበሰ የሠራዊት አባል ነው፤

12/ “ግዳጅ” ማለት ማንኛውም የሠራዊት አባል ቃለ መሃላ ፈጽሞ የቅጥር ውል ከፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ከሠራዊት እስከሚሠናበትበት ጊዜ ድረስ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ  ውስጥ የሚያከናውነው የውትድርና ተግባር ነው፤

13/ “በክብር የተሰናበተ“ ማለት ማንኛውም ዓይነት የዲሲፕሊን ጉድለት ሳይኖርበት ተልዕኮውን በአግባቡ ተወጥቶ በመከላከያ ሠራዊቱ አሰራር መሰረት በአግባቡ የተሰናበተ ነው፤

14/ “የጦር ሜዳ ግዳጅ” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአገር አቀፍ ደረጃ የጦርነት ወይም የክተት አዋጅ ሲታወጅ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በሙሉም ሆነ በከፊል የጦርነት አደጋ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ ሲሰጥ ወይም ሠራዊቱ በጦርነት ግዳጅ ላይ እንደሆነ ሲወሰን ወይም በህጉ መሠረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚከናወን የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ ሆኖ እንደየሁኔታው በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር ሊፈጸም ይችላል፤

15/ “የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አባል” ማለት በህግ መሰረት ለብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አባልነት ተመልምሎ አስፈላጊውን ስልጠና ከወሰደ በኋላ የውትድርና አገልግሎት ለመስጠት የሚጠባበቅ ሰው ነው፤

16/ “ወታደራዊ የፍትህ አካላት” ማለት ወታደራዊ ፖሊስ፣ ወታደራዊ መርማሪ፣ ወታደራዊ አቃቤ ህግ፣ ወታደራዊ ፍርድ ቤት እና ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃን ያካተተ የጋራ መጠሪያ ነው፤

17/ “የፌደራልና የክልል ጸጥታ ኃይሎች” ማለት የፌደራል ወይም የክልል ፖሊስ፣ ሚሊሻ፣ የአገር ውስጥ ደህንነት፣ የፀረ-ሽብር፣ የጉምሩክ፣ የኢሚግሬሽን ሃይሎችና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተመሳሳይ ስራ የሚያከናውኑ አካላት ናቸው፤

18/ “መደበኛ የፍትህ አካላት” ማለት የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ፣ እና ማረሚያ ቤቶችን ያጠቃልላል፤

19/ “የሰላም ማስከበር ተልዕኮ” ማለት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወይም በአፍሪካ ህብረት ውሣኔ ወይም በአጋር አገራት ወታደራዊ ትብብር በውጭ አገር የሚከናወን የሰላም ማስፈን ወይም የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ነው፤

20/ "ሲቪል" ማለት ከመከላከያ ሠራዊት አባል ውጪ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

21/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ላይ እንዲሁም እንደአግባብነቱ በሲቪሎችም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ወታደራዊ አገልግሎት

## 4. ስለ መከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት

1/ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በሁሉም አውዶች ማለትም በምድር፣ በአየር፣ በባህር፣ በሳይበርና በጠፈር/ስፔስ መዋጋት በሚችል መልኩ ይደራጃል፣

2/ በአውዶቹ መሰረት የሚኖሩ አደረጃጀቶች እንዳስፈላጊነቱ የልዩ ዘመቻዎች ኃይልና ተጠባባቂ ኃይል ሊኖራቸው ይችላል፣

3/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደየግዳጁ አስፈላጊነት በውስጡ ንዑሳን አደረጃጀቶችን ሊያዋቅር ይችላል፣

## 5. የመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮዎች

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊቱ የሚከተሉት ተልዕኮዎች ተሰጥተውታል፣

1/ የሀገርን ሉአላዊነት፣ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ከውጭ ወራሪና ከውስጥ ፀረ-ሠላም ኃይሎች ስጋትና ጥቃት በአስተማማኝ ሁኔታ መከላከል፣

2/ አግባብነት ካላቸው የፌደራልና የክልል መስተዳድሮች የደህንነትና የፀጥታ መዋቅሮች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፣

3/ የህዝብን ህይወት፣ የህዝብ እና የመንግስት የልማት ተቋማትንና አውታሮችን ከማናቸውም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች መከላከልና ማዳን፣

4/ በአካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የሠላም ማስከበር ግዳጅ/ተግባራት ላይ በብቃት መሳተፍ፣

5/ በማንኛውም ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን ተልዕኮዎች ለመፈፀም የሚያስችሉ የሠራዊት ግንባታ ተግባራትን በማከናወን ብቁና ዝግጁ ሠራዊት መገንባት፤

## 6. ስለመመልመል

1/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየጊዜው በሚያወጣው መመዘኛ መሰረት ለወታደርነት ብቁና ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ሊመለምል ይችላል፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያደርገው ምልመላ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ሚዛናዊ ተዋፅዖ ያካተተ ይሆናል፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የእጩ መኮንንነት ምልመላ ከሠራዊት አባላትና በቀጥታ ከሲቪል ህብረተሰብ ይካሄዳል።

4/ ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ለሁለት ዓመታት በሠራዊቱ ብሔራዊ ግልጋሎት ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ አባላትን ተቋሙ ተቀብሎ ግልጋሎት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል። አባላቱ ግልጋሎታቸውን ሲጨርሱ የብሔራዊ

ተጠባባቂ ኃይል አባላት የሚሆኑ ከሆነ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተያያዥ መብቶችና ጥቅሞች እንዲጠበቁላቸው ያደርጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይገለፃል፣

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (4) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተቋሙ ተልዕኮ አስፈላጊ ናቸው ተብለው በሚለዩ ሙያዎች ተቋሙ ፈቃደኛ የሆኑ ሙያተኞችን መልምሎ በብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይልነት ሊይዝ ይችላል።

## 7. ስለ ቅጥር

ለወታደርነት የተመለመለ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የቅጥር ውል ይፈጽማል።

## 8. ወታደራዊ ሥልጠና

1/ ለወታደርነት የተመለመለ ማንኛውም ሰው የውትድርና አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የውትድርና ሥልጠና ይሰጠዋል፣

2/ በአገልግሎት ላይ ያለ የሠራዊት አባል እንደየግዳጁ አስፈላጊነት ዝንባሌውና ችሎታው እየተመዘነ በልዩ ልዩ የሙያ መስክ እንዲሰለጥን ወይም እንዲማር ሊደረግ ይችላል፣

3/ ማንኛውም ለመኮንንነት የተመለመለና መስፈርቱን ያሟላ አባል በመኮንንነት ለማገልገል የሚያስችለው የዕጩ መኮንንነት ሥልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፣ ስልጠናውን በስኬት ካጠናቀቀም የምክትል የመቶ አለቃ ማዕረግ ይሰጠዋል፣

4/ ወታደራዊ የሥራ ኃላፊነት ወይም የማዕረግ ዕድገት በሚሰጥበት ጊዜ የሠራዊት አባሉን ለቦታውና ለደረጃው ብቁ የሚያደርገው ሥልጠና ወይም ትምህርት ሊሰጠው ይችላል፣

5/ የማዕረግና የኃላፊነት እድገት ሲሰጥ ብቃትን መሰረት ባደረገ ውድድር በሠራዊቱ ውስጥ የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ሚዛናዊ ተዋፅዖና የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል።

## 9. ወታደራዊ ቃለ መሐላ

1/ ማንኛውም ምልምል ወታደር መሰረታዊ የውትድርና ሥልጠናውን እንዳጠናቀቀ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ወታደራዊ ቃለ-መሐላ ይፈፅማል፣

2/ ማንኛውም አባል መኮንን ሲሆን ቃለ-መሐላ ይፈፅማል፣

## 10. የሠራዊት አባላት ግዴታ

ማንኛውም የሠራዊት አባል፡-

1/ የአገሪቱን ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር የመጠበቅና የመከላከል ግዴታ አለበት፣

2/ ሕገ-መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፣

3/ የአገሪቱን ህጐች፣ ወታደራዊ ህጐች፣ መመሪያዎችና ቋሚ ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለበት፣

4/ የአገር ፀጥታ አስጊ ሁኔታ ላይ ይወድቃል ተብሎ በአገር ደረጃ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ ሲሰጥ ወይም ተጨባጭ ጦርነት ሲኖር ከውትድርና አገልግሎት ዘመኑ ውጪም ቢሆን በአገልግሎት ላይ የመቆየት ግዴታ አለበት፣

5/ አግባብ ባለው ደንብ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ተመድቦ የመስራት ግዴታ አለበት፣

6/ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኋን የማከናወን ግዴታ አለበት፣

## 11. የውትድርና አገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ እድሜ

1/ ማንኛውም የሠራዊት አባል ለውትድርና አገልግሎት ሲቀጠር ቢያንስ ለ7 ዓመታት ማገልገል አለበት።

2/ ማንኛውም የሠራዊት አባል መኮንን ከሆነ በኋላ ወይም የልዩ ሙያ ባለቤት ከሆነ ቢያንስ ለ10 ዓመታት የማገልገል ግዴታ አለበት፣ ሚኒስቴሩ በልዩ ሙያ የሚያካትታቸው ሙያዎች ዝርዝር በመመሪያ ይገለፃል።

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሠራዊት አባሉ ተጨማሪ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነና ሚኒስቴሩ ከተስማማ የአገልግሎት ጊዜው ለተጨማሪ 7 እና 10 ዓመታት ሊራዘም ይችላል።

4/ በአገር ደረጃ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ ባይሰጥም ወይም ተጨባጭ ጦርነት ባይኖርም ሚኒስቴሩ የደህንነት ስጋት አለ ብሎ ሲያምን የ7 እና የ10 አመት የስንብት ጥያቄን እስከ ሶስት ዓመት ሊያራዝም ይችላል።

5/ የማንኛውም የሠራዊት አባል የጡረታ መውጫ እድሜ የሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ከመሰረታዊ ወታደር እስከ ሃምሳ ዓለቃ ወይም ተመጣጣኝ ማዕረግተኛ 45 ዓመት፤

ለ) ከመጋቢ ሃምሳ ዓለቃ እስከ ሻለቃ ባሻ ወይም ተመጣጣኝ ማዕረግተኛና መስመራዊ መኮንን 48 ዓመት፤

መ) ዋራንት ኦፊሰር ወይም ተመጣጣኝ ማዕረግተኛና ከፍተኛ መኮንን 52 ዓመት፤

ሠ) ብርጋዴር ጄነራልና ተመጣጣኝ ማዕረግተኛ 56 ዓመት፤

ረ) ሜጀር ጄነራልና ተመጣጣኝ ማዕረግተኛ 57 ዓመት፤

ሸ) ሌተናል ጄነራልና ተመጣጣኝ ማዕረግተኛ 58 ዓመት፤

ቀ) ጄነራልና ተመጣጣኝ ማዕረግተኛን ጨምሮ ፊልድ ማርሻል 60 ዓመት፤

6/ ሚኒስቴሩ ለግዳጅ አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የሠራዊት አባላት የጡረታ መውጫ እድሜ በየሁለት ዓመቱ ለሁለት ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

7/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን የፊልድ ማርሻል የጡረታ እድሜ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ውሳኔ መሰረት ላልተወሰነ ጊዜ ሊራዘም ይችላል።

8/ የጡረታ መውጫ እድሜ የሚራዘመው፡-

ሀ) የአባሉ ትምህርት፣ ልዩ ዕውቀት፣ ችሎታና ልምድ ለሚኒስቴሩ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) በደረጃ ዕድገት ወይም በውስጥ ዝውውር ክፍተቱን ለመሸፈን አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤

ሐ) አባሉ ለስራው ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

መ) አባሉ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ ይሆናል።

9/ የጡረታ መውጫ እድሜን የማራዘም ስልጣን

ሀ/ የኤታማዦር ሹሞ፣ የምክትል ኤታማዦር ሹም እና የኃይል አዛዦችን የጡረታ መውጫ እድሜ የማራዘም ስልጣን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይሆናል።

ለ/ ከኤታማዦር ሹሞ፣ ከምክትል ኤታማዦር ሹም እና ከኃይል አዛዦች ውጪ የሆኑትን የሠራዊት አባላት የጡረታ መውጫ እድሜ የማራዘም ስልጣን የኤታማዦር ሹም ይሆናል።

## 12. አገልግሎቶችን ስለማግኘት

1/ በሠራዊቱ ውስጥ በውትድርና አገልግሎት ላይ የሚገኝ ማንኛውም የሠራዊት አባል አግባብ ባለው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውስጥ ደንብና መመሪያ መሰረት ቀለብ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የደንብ ልብስ፣ የመጓጓዣና የሕክምና አገልግሎት በነፃ ያገኛል፣

2/ በአገልግሎት ላይ ያለ ማንኛውም የሠራዊት አባል በሱ አማካኝነት የመታከም መብት ያገኙ የቤተሰቡ አባላት ወይም የአገልግሎት ወይም የጉዳት ወይም የህመም ጡረታ መብት ተከብሮላቸው ከአገልግሎት የተሰናበቱ ከፌደራልና ከክልል መንግስታት ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኙ የመንግስት የህክምና ተቋማት በነፃ የመታከም መብት ይኖራቸዋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## 13. ለሠራዊት አባላት ስለሚደረግ ማበረታቻ

የመከላከያ ሠራዊት አባላት ወታደራዊ አገልግሎታቸውን በላቀ ሞራል እንዲያከናውኑ ለማበረታታት፣

1/ ሰላሳ ዓመትና ከዚያ በላይ ያገለገለ የሠራዊት አባል አንድ የቤት መኪና ከቀረጥና ግብር ነፃ መግዛት ይችላል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

2/ ሰላሳ ዓመት እና ከዛ በላይ ያገለገሉ የሠራዊት አባላት የግል ቤት የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ በተወለዱበት የክልል ከተሞች ውስጥ የግል የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ መንግስት ድጋፍ ያደርጋል፣ በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት መገንባት እንዲችሉ የገንዘብ ድጎማ ያደርጋል። የገንዘብ ድጎማው መጠን ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለጀነራል መኮንን በአዲስ አበባ ይሆናል፣

4/ በአገልግሎት ላይ ያለ ማንኛውም የሠራዊት አባል የሠራዊቱን መለያ ልብስ እስከለበሰና መታወቂያ ካርዱን እስከያዘ ድረስ በመንግስትም ሆነ በግል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በቅድሚያ አገልግሎት ያገኛል፣

5/ በአገልግሎት ላይ ያለ ማንኛውም የሠራዊት አባል የሠራዊቱን መለያ ልብስ እስከለበሰና መታወቂያ ካርዱን እስከያዘ ድረስ በመንግስት የልማት ድርጅቶች በግሉ ለሚያገኘው አገልግሎት የ 10% የአገልግሎት ክፍያ ቅናሽ ተጠቃሚ ይሆናል፣

6/ የመከላከያ ሚኒስቴር የግል አገልግሎት ሰጪና የንግድ ተቋማትም በበጎ ፈቃደኝነት ለመከላከያ ሠራዊት አባላት የቅናሽ፣ የእውቅና እና የማበረታቻ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

7/ በአገልግሎት ላይ ያለ ማንኛውም የሠራዊት አባል የሠራዊቱን መለያ ልብስ እስከለበሰ ወይም መታወቂያ ካርዱን እስከያዘ ድረስ በመንግስት ባለቤትነት በተያዙ የህዝብ የከተማ አውቶቡስና ቀላል ባቡር የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በነፃ ያገኛል፣

8/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሠራዊቱን ኑሮ የሚያሻሽሉ፣ የሠራዊቱን የውጊያ ዝግጁነት የሚያጎለብቱ፣ ሚኒስቴር መስያ ቤቱን በተለያዩ ተግባራት የሚደግፉ፣ ለተቋሙም ይሁን ለአገር ኢኮኖሚ ፋይዳ ያላቸው የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽንን ጨምሮ በተቀጣጣሪ ባለስልጣንነት የሚመራቸውን ሌሎች የልማት ድርጅቶችን ሊያቋቁም ይችላል።

## 14. የውትድርና አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

1/ የሚከተሉት የውትድርና አገልግሎት የሚያቋርጡ ምክንያቶች ናቸው፡-

ሀ) የቅጥር ውሉ ዘመን ሲያበቃ፤

ለ) ሲሞት፤

ሐ) አባሉ የአገልግሎት የውል ጊዜው ሳይጠናቀቅ የስንብት ጥያቄ አቅርቦ ስንብቱ ሲፀድቅ፤

መ) አገልግሎት ለመቀጠል የማያስችል ከባድ ሕመም ወይም የአካል ጉዳት ደርሶበት ለውትድርና አገልግሎት ብቁ አለመሆኑ በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ፤

ሠ) በጡረታ ሲገለል፤

ረ) በጠላት ተማርኮ አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ወይም ከጠላት ጋር በተደረገ ውጊያ መሃል ጠፍቶ ከ6 ወራት ላላነሰ ጊዜ ሁኔታው ያልታወቀ ሲሆን፤

ሰ) በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የመዋቅር ለውጥ፣ ወይም የአሰራር ማሻሻያ በመደረጉ ምክንያት በአገልግሎት እንዲቀጥል ለማድረግ ሳይቻል ሲቀር፤

ሸ) በመደበኛ የውትድርና ሥራ አፈፃፀም ወይም በአመራር ብቁ ባለመሆን ወይም በዲስፕሊን ጉድለት ለአገልግሎት አስፈላጊ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ፤

ቀ) በወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ጥፋተኛ የተባለና ሁለት ዓመትና ከዛ በላይ የእስር ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን፤

በ) የእስር ቅጣት ፍርዱ ከሁለት ዓመት በታች ቢሆንም ግለሰቡ የተፈረደበት ኩብለላ፣ ክዳት፣ ወይም ሌሎች ለህሊና እና ሞራል ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶች በመፈፀሙ ከሆነ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ቀ) የተደነገገው ቢኖርም ጥፋተኛው ወንጀሉን የፈጸመው የተሰጠውን ግዳጅ በመፈጸም ላይ እያለ ከሆነ ወይም የሰው ህይወት ወይም ንብረት ለመከላከል ሲል ከሆነ፣ ወይም በመልካም ስነ-ምግባሩ ምስጉን የነበረና ከአስር ዓመት በላይ በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ያገለገለ ከሆነ ከሁለት ዓመት በላይ እስር የተፈረደበት ቢሆንም ከእስር ሲፈታ ወደ አገልግሎት እንዲመለስ ሊደረግ ይችላል።

## 15. በሀገራዊ ዳግም ጥሪ ስለማገልገል

1/ ማንኛውም በክብር የተሰናበተ የሠራዊት አባል የሀገር ሉዓላዊነትን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲያጋጥም አደጋውን ለመመከት መንግስት ወይም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዳግም ጥሪ ሲያደርግ ለጥሪው ምላሽ የመስጠትና ሀገራዊ ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት ይኖረዋል፣

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተገለፀው አግባብ በዳግም ጥሪው መሰረት ወደሠራዊቱ የተቀላቀለ የሠራዊት አባል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በቀጣይነት እንዲያገለግል በነበረበት የማዕረግ ደረጃ መልሶ ሊቀጥረው ይችላል፣

## 16. ስለአገልግሎት ካሣና ጡረታ

1/ አንድ የሠራዊት አባል የውል ግዴታ የገባበትን የአገልግሎት ዘመን ጨርሶ ከሥራ ሲሰናበት ሚኒስቴሩ መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ካሳ ይከፈለዋል፣

2/ አንድ የሠራዊት አባል የውል ግዴታ የገባበት የአገልግሎት ዘመን ከማለቁ በፊት በራሱ ፈቃድ ወይም ጉድለት ሳይሆን በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎቱ ቢቋረጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተገቢውን ካሣ ያገኛል፣

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) የተመለከቱት የሥራ መሰናበቻ ዕድሜ ጣሪያዎች ለጡረታ ህግ አፈፃፀም የጡረታ መገለያ ዕድሜ ሆነው ይቀጠራሉ፣

4/ በውትድርና አገልግሎት ላይ በደረሰ ጉዳት ወይም በስራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ በዘላቂነት ለውትድርና አገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ወይም በጉዳቱ ምክንያት አባሉ የሞተ እንደሆነ መብቱ በመንግስት ሰራተኞች የጡረታ ህግ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

5/ በግዳጅ ላይ የተሰዋ የሠራዊት አባል የጡረታ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ለህጋዊ ወራሾቹ ወርሀዊ ደመወዙ እየተከፈለ ይቀያል፣ ይሁን እንጂ የጡረታ ሂደቱ በሶስት ወራት ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

6/ አንድ የሠራዊት አባል በውትድርና አገልግሎት ላይ እያለ በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት እራሱን መርዳት የማይችል መሆኑ በተቋሙ የሚዲካል ቦርድ ሰረጋገጥ በመንግስት በሚቋቋም የጀግኖች አምባ በዘላቂነት እንዲጦር ይደረጋል።

## 17. ስለ ፈቃድ

ማንኛውም የሠራዊት አባል ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የዓመት እረፍት ፈቃድና ልዩ ልዩ ፈቃዶች ይሰጠዋል።

## 18. ስለወታደራዊ ዲሲፕሊን

ማንኛውም የሠራዊት አባል በወታደራዊ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ቋሚ ትእዛዞች ውስጥ የተመለከቱትን የተላለፈ እንደሆነና ጥፋቱ አነስተኛ በመሆኑ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚያስቀርበው ካልሆነ ጉዳዩ በሠራዊቱ አስተዳደር ደንብ መሰረት እንዲታይ ይደረጋል።

## 19. አቤቱታ ስለማቅረብ

ማንኛውም የሠራዊት አባል የአስተዳደር በደል የደረሰበት እንደሆነ ወይም በተወሰነበት የዲሲፕሊን ቅጣት ቅሬታ ያደረበት እንደሆነ በሠራዊቱ የዲሲፕሊን ደንብ መሰረት አቤቱታ የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት ይኖረዋል። በየደረጃው የሚገኙ የሠራዊቱ አዛዦችም የሠራዊቱ አባላት ለሚያቀርቡት አቤቱታ በህግ መሰረት በወቅቱ ውሳኔ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል ሦስት

## ስለማዕረግ እድገት፣ ስለአገልግሎትና ስንብት

## 20. የማዕረግ ደረጃዎች

የምድር ኃይል፣ የአየር ኃይልና የባህር ኃይል ወታደራዊ የማዕረግ ደረጃዎች  ዝርዝር በደንብ ይወሰናል።

## 21. ስለማዕረግ እድገት አሰጣጥ

1/ በወታደራዊ ግዳጅ አፈፃፀም፣ በሥነ ሥርዓት አክባሪነት፣ በአመራር ችሎታና ብቃት ብልጫ ያሳየ የሠራዊት አባል ክፍት የመሾሚያ ቦታ ሲኖር ሚኒስቴሩ ስለማዕረግ ዕድገት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የማዕረግ እድገት ይሰጠዋል፣

2/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም፣ የአዛዦች ምክርቤት፣ ኃይል አዛዥ፣ ዕዝ አዛዥ፣ የዋና መምሪያና አቻ ክፍሎች ኃላፊዎች የማዕረግ እድገት የመስጠት ወይም የማፅደቅ ስልጣን ይኖራቸዋል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

3/ የጀነራል መኮንኖችና የፊልድ ማርሻል የማዕረግ እድገት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ መልምለው ብቁ መሆናቸውን አረጋግጠው ሲያቀርቡ በርዕሰ ብሔሩ የሚፀድቅ ይሆናል፣

## 22. የግዴታ አገልግሎት

1/ ማንኛውም የሠራዊት አባል ልዩ ሥልጠና ወይም ትምህርት ተከታትሎ ከጨረሰ በኋላ በስልጠና ወይም በትምህርት የቆየበትን ጊዜ እጥፍ የማገልገል ግዴታ አለበት፣

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሙያዎቹ ልዩ ባህሪና ከሚያስከትሉት ከፍተኛ ወጪ አኳያ የልዩ ሙያተኞች የአገልግሎት ውል ግዴታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 23. ከውትድርና አገልግሎት የማሰናበት ስልጣን

የጡረታ መውጫ እድሜ ከመድረሱ በፊት በመዋቅር ለውጥ፣ በአሰራር ማሻሻያ፣ በአቅም ማነስ ወይም በመሳሰሉት ምክንያቶች አገልግሎቱ የሚቋረጥና የሚሰናበት፣

1/ ጀነራል መኮንን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣

2/ መስመራዊና ከፍተኛ መኮንኖች በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም፣

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌተናል ኮሎኔልና ኮሎኔል ስንብት ላይ የአዛዦች ምክርቤት አስተያየት እንዲሰጥበት ይደረጋል፣

4/ የበታች ሹሞች በሰው ኃብት አመራር ዋና መምሪያ በኩል የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምን በማማከር ስንብቱ በኃይሎችና በዕዞች ይፈፀማል።

## 24. ወደሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ስለሚደረግ ዝውውር

1/ መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የሠራዊት አባል ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት በቋሚነት ማዛወር ይችላል፣

2/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና ተቀባዩ መሥሪያ ቤት እንዲሁም የሚዛወረው አባል ሲስማሙ አንድን የሠራዊት አባል ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት በቋሚነት ማዛወር ይችላል፣

3/ መንግስት ወይም ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የመከላከያ ሠራዊት አባል ወደ ሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ለተወሰነ ጊዜ አዛውሮ ማሠራት ይችላል፣

4/ ከሚኒስቴሩ ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት በቋሚነት የተዛወረ የሠራዊቱ አባል መብቱና ግዴታው የተዛወረበት መስሪያ ቤት በሚተዳደርበት ህግ የሚገዛ ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የሚኒስትሩ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምና የመከላከያ አዛዦች ምክርቤት ሥልጣንና ተግባር

### 25. የሚኒስትሩ ስልጣንና ተግባር

ሚኒስትሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ሠራዊቱ ለህገመንግስቱ ተገዥ መሆኑንና ለህገ መንግስቱ መከበር በጽናት መቆሙን ያረጋግጣል፤

2/ መከላከያን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊመከርባቸውና ሊወሰኑ የሚገባቸውን ጉዳዮች እያቀረበ ያስወስናል፤

3/ ሠራዊቱ የሚተዳደርባቸውን ህጐች፣ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቁም በተግባር ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

4/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በተግባር መዋሉን ይቆጣጠራል፤

5/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተቆጣጣሪ ባለስልጣንነት የሚመራቸውን የልማት ድርጅቶችና የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽንን ይቆጣጠራል፤ በማቋቋሚያ ህጎቻቸው ላይ የተደነገገውን ሃላፊነቶቻቸውን እየተወጡ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፤

6/ መከላከያን በተመለከተ ከውጭ አገር መንግስታትና መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

7/ በመንግስት ውሳኔ መሰረት አገር አቀፍ የክተት ዘመቻዎችን ያስተባብራል፤

8/ የሠራዊቱን አቅም የሚገነቡ የከፍተኛ ትምህርት፣ የጥናትና ምርምር ተቋሞችና አቅሞችን ያደራጃል፣ ይመራል፤

9/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል።

### 26. የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሥልጣንና ተግባር

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያን በበላይነት ይመራል፤ የአዛዦች ምክር ቤትን ይሰበስባል፣

2/ የሀገርን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ያስከብራል፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያስፈፅማል፤ ከክልል መስተዳድር አቅም በላይ የሆነ የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም ሁኔታውን ለመቆጣጠር ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

3/ የአገር ደህንነትና ሉዓላዊነትን ለማስከበር በሚያስችል መልኩ የአገር መከላከያ ሠራዊትን ያደራጃል፤

4/ ሠራዊቱ በማንኛውም ጊዜ ለውጊያ ብቁና ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፤

5/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ መመሪያና ውሳኔን መሰረት በማድረግ ሠራዊቱን ያዛል፣ ያዋጋል፤

6/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥና ሚኒስትሩን በወታደራዊ ጉዳዮች ላይ ያማክራል።

## 27. የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማዦር ሹም ሥልጣንና ተግባር

የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማዦር ሹም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም በሌለበት ተክቶ ይሰራል፤

2/ ከጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የዋና መምሪያዎችን ተግባራት ያስተባብራል፣

3/ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## 28. የመከላከያ አዛዦች ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የመከላከያ አዛዦች ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ በኦፕሬሽናልና በስትራተጂክ እቅዶችና በሠራዊቱ አደረጃጀት ላይ ተወያይቶ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፤

2/ በሠራዊቱ የበጀት ድልድል ላይ ኃሳብ ያቀርባል፤

3/ ለብርጋዴር ጀነራልነት ማዕረግ በእጩነት በሚቀርቡት ላይ መክሮ ኃሳብ ይሰጣል፤

4/ ለሌተናል ኮሎኔልነትና ለኮሎኔልነት ማዕረግ የታጩ መኮንኖች የስራ አፈፃፀም ሁኔታ ላይ ተወያይቶ ኃሳብ ይሰጣል፣ የማዕረግ እድገት ያፀድቃል፤

5/ ለሜጀር ጀነራልነት ማዕረግ በታጩ አባላት ጉዳይ ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምን ሊያማክር ይችላል፣

6/ የጡረታ መውጫ እድሜው ከመድረሱ በፊት በአቅም ማነስ፣ በመዋቅር ለውጥ፣ በአሰራር ማሻሻያና በመሳሰሉት ምክንያቶች የሚሰናበት ሌተናል ኮሎኔል ወይም ኮሎኔል ስንብት ላይ መክሮ ኃሳብ ይሰጣል፤

7/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምን በወታደራዊ ጉዳዮች ያማክራል።

## 29. የመከላከያ አዛዦች ምክር ቤት አባላት

1/ የመከላከያ አዛዦች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ) የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም (ሰብሳቢ)፣

ለ) የጦር ኃይሎች ምክትል ኤታማዦር ሹም (አባል)፣

ሐ) የኃይል አዛዦች (አባል)፣

መ) የዋና መምሪያ ኃላፊዎች (አባል)፣

ሠ) የዕዝ አዛዦች (አባል)፣

ረ) ኢንስፔክተር ጀነራል (አባል)፣

2/ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ እንደስራው አስፈላጊነት ካለድምጽ የሚሳተፉ ተጨማሪ የልዩ ልዩ የሠራዊት ክፍል አዛዦች በምክር ቤቱ ስብሰባ እንዲገኙ ሊጠራ ይችላል።

## ክፍል አምስት

## ስለወታደራዊ ፍትህ አካላት

### 30. መቋቋም

በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የወታደራዊ ፍትህ ሥራን የሚያከናውኑ የሚከተሉት አካላት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1/ ወታደራዊ ፖሊስ፤

2/ ወታደራዊ መርማሪ፤

3/ ወታደራዊ ዓቃቢ ህግ፤

4/ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች፤ እና

5/ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ።

### 31. የወታደራዊ ፖሊስ ስልጣንና ተግባር

የወታደራዊ ፖሊስ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ በሠራዊቱ ውስጥ ወንጀል እንዳይፈጸም ይከላከላል፤

2/ የወታደራዊ ካምፖችና የሠራዊቱ ቢሮዎችን ደህንነትና ሥነ-ሥርዓት ያስከብራል፤

3/ የሠራዊቱን የማረሚያ እና ማቆያ ስፍራዎች ያስተዳድራል፣ ታራሚዎችን ይገነባል፤

4/ የወታደራዊ ወይም የመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም የአዛዦች ውሣኔዎችና ትዕዛዞችን ያስፈጽማል።

### 32. ስለጥቆማ

1/ ማንኛውም የሠራዊት አባል ወታደራዊ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ ሲገኝ ለቅርብ አመራሩ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ወታደራዊ ወይም መደበኛ ፖሊስ ወይም ለዓቃቢ ህግ ጥቆማ የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

2/ በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን የሚወድቅ ወንጀል በሠራዊት አባል የተፈጸመበት ተበዳይ ወታደራዊ ዓቃቢ ህግ በጉዳዩ ላይ ክስ ካልመሠረተ ክሱን በግሉ ለወታደራዊ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥቆማ የቀረበለት አዛዥ፣ መርማሪ ወይም ዓቃቢ ህግ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ በወንጀል ሥነ-ስርዓት ህግና በዚህ አዋጅ የሚጠበቅበትን ተግባር መፈፀም አለበት።

## 33. ተጠርጣሪን ስለመያዝ

1/ በአገሪቱ የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግና በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተጠርጣሪን የያዘ ማንኛውም የሠራዊት አባል አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ በአቅራቢያው ለሚገኝ የጦር ክፍል አመራር ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሪፖርት የደረሰው አዛዥ ሕግን ተከትሎ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ ለወታደራዊ መርማሪ ወይም ለመደበኛ ፖሊስ ተጠርጣሪውን ማስረከብ አለበት፣

3/ በወታደራዊ ካምፖች፣ ቢሮዎች፣ ወይም በግል የሠራዊት መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ጊዜ የማይሰጥና አደገኛ ወንጀል ወይም የፀጥታ መደፍረስ ሲከሰት ወይም ይከሰታል የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖር በየደረጃው ያለ አዛዥ እስር ወይም ብርበራ ማካሄድ ይችላል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የተፈፀመ እስር ወይም ብርበራ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ያለበት ሆኖ ለማጓጓዝ ያለውን ጊዜ ሳይጨምር በ48 ሰዓት ውስጥ የታሰረውን ሰውና በብርበራ የተያዘውን ንብረት ለፍርድ ቤት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ለመደበኛ ፖሊስ መቅረብ አለበት።

## 34. ስለ ወታደራዊ መርማሪ

1/ ወታደራዊ ወንጀል መርማሪ፣ የሬጅመንት ወይም የሻለቃና ከዚያ በላይ ያለ አዛዥ የወንጀል ድርጊት ሲፈፀም ወይም ተፈፅሟል የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ምርመራ የመጀመር ወይም የማስጀመር ኃላፊነት አለበት፣

2/ በወንጀል መርማሪውና በአዛዡ መካከል ምርመራን ስለመጀመር ወይም ስለማቋረጥ ልዩነት ከተፈጠረ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ያለ አዛዥ ውሳኔ ይሰጥበታል። ውሳኔ ሰጪው አዛዥ ወንጀል ምርመራውን አስመልክቶ የሚሰጣቸውን ምርመራ የማስጀመር ወይም የማቋረጥና ሌሎች ተያያዥ ውሳኔዎችን በፅሁፍ ለወንጀል ምርመራ ክፍሉ የመስጠት ግዴታ አለበት፣

3/ አዛዡ ምርመራን ለማቋረጥ የሰጠው ትዕዛዝ ህገወጥ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፣

4/ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህግና በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ጥልቅና ገለልተኛ በሆነ ምርመራ መጣራት አለበት፣

5/ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚታይ ማንኛውም ወንጀል በየደረጃው በተደራጀ የወታደራዊ ወንጀል ምርመራ ክፍል ወይም በልዩ ሁኔታ ሊደራጅ በሚችል የምርመራ ቡድን ወይም በመደበኛ ፖሊስ እንዲጣራ ይደረጋል፣

6/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት በመደበኛ ፖሊስ ወይም በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የሚወድቁ ወንጀሎች በካምፖች ወይም በወታደራዊ ይዞታዎች ተፈጽመው ሲገኙ አዛዦች ወይም ወታደራዊ መርማሪዎች በቀላሉ ሊጠፉ የሚችሉ ማስረጃዎችን በመሰብሰብና የቅድመ ምርመራ ሥራዎችን በማከናወን ውጤቱን ለሚመለከተው መደበኛ ፖሊስ ያስረክባሉ።

## 35. ስለእስር ቅጣት አፈፃፀም፣

1/ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ከሁለት ዓመት በታች ቅጣት የተወሰነባቸው የሠራዊት አባላት በወታደራዊ ማረሚያ ቤት፣ ሁለት ዓመትና ከዛ በላይ ቅጣት የተወሰነባቸው የሠራዊት አባላት ደግሞ በመደበኛ ማረሚያ ቤት ይታረማሉ፣

2/ የታራሚዎች የዝውውር ወይም የይቅርታ ወይም የምህረት ጥያቄዎችና ሌሎች ተዛማጅ መብቶች ታራሚው ባለበት መደበኛ ወይም ወታደራዊ ማረሚያ ቤት ይፈጸማል።

## 36. የወታደራዊ ዓቃቢ ሥልጣንና ተግባር፣

ወታደራዊ ዓቃቢ ህግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር በሚወድቁ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች ላይ ክስ ያቀርባል፣ ይከራከራል፤

2/ የወንጀል ክስ ለመመስረት ሲወስን ለሚመለከተው አዛዥ ሪፖርት ያደርጋል፣ በጉዳዩ ላይ ያማክራል፤

3/ የወንጀል ምርመራን ይመራል፣

4/ በተቋማዊ የህግ ማዕቀፎች ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥናት ያደርጋል፣ ስልጠና ይሰጣል፣ ኃሳብ ያመነጫል፣ ለውሳኔ ያቀርባል፣

5/ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ የተቋሙን መብትና ጥቅም በሚመለከት ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣

6/ በወታደራዊ ማረሚያ ቤት ቁጥጥር ስር ያሉ አባላትን ይጎበኛል፣ አያያዛቸውን በሚመለከት ጉድለቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

7/ በተቋማዊ ሰብአዊ መብት አጠባበቅ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ተግባራትን ያከናውናል፣

## 37. የወታደራዊ ወንጀል ክስ እንዲቋረጥ የማዘዝ ስልጣን

1/ ሚኒስትሩ የሚከተሉት መስፈርቶች ከተሟሉ በወንጀል ህጉ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ክሶች እንዲቋረጡ ሊያዝ ይችላል፡-

ሀ) ተከሳሽ በወታደራዊ የወንጀል ድርጊቱ የተፀፀተ እንደሆነ፤

ለ) ክሱ ቢቋረጥ በተቋሙም ሆነ በአገር ላይ የሚያስከትለው ከፍ ያለ ጉዳት አይኖርም ተብሎ የሚገመትና ተከሳሹ መልካም ዜጋ ሆኖ ለተቋሙ ወይም ለአገር በጎ አስተዋፅዖ ያበረክታል ተብሎ እምነት የሚጣልበት ከሆነ፤

ሐ) የተከሳሽ የዘወትር ባህሪው መልካም የነበረና የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ የሌለበት ከሆነ፤ እና

መ) ወታደራዊ ወንጀሉ ከተቋሙ ገንዘብ ወይም ንብረት ጋር የተያያዘ ከሆነና ተከሳሹ በገንዘብ ወይም በአይነት ወይም በአገልግሎት ለተቋሙ ካሳ የከፈለ ወይም ለመካስ የሚፀና ቃል የገባ እንደሆነ።

2/ ወታደራዊ ወንጀሉ ከሌላ መደበኛ ወንጀል ጋር ተጣምሮ ክስ የተመሰረተበት ከሆነ ክስ የማቋረጥ ትዕዛዙ ለወታደራዊ ወንጀሉ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፣

3/ የወታደራዊ ወንጀል ክስ እንዲቋረጥ የሚሰጥ ውሣኔ ምክንያቱ ተጠቅሶ በፅሁፍ ካልተገለፀ በቀር ተቀባይነት አይኖረውም።

## 38. ስለ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ

1/ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ በወንጀል ተጠርጥረው በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ምርመራ ለሚደረግባቸው ወይም ለተከሰሱ ሰዎች የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣል፣

2/ ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ በፍርድ ቤት ተከሳሽን ወክሎ የተከራከረበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚም ሆነ በሰበር ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ አገልግሎቱን የመስጠት ኃላፊነት አለበት፣

3/ ማንኛውም የሠራዊት አባል ወይም የመከላከያ ሲቪል ሠራተኛ የመከላከያ ወይም የመንግስት ግዳጅ በመፈፀም ላይ እያለ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ በወንጀል ተከሶ በፌደራል ወይም በክልል መደበኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ  ተከላካይ ጠበቃ ይመደብለታል፣

4/ በወንጀል ተጠርጥሮ በወታደራዊ ፍርድ ቤት የተከሰሰ ሰው በመረጠው ጠበቃ የመወከል መብት ይኖረዋል፣

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው ቢኖርም ለአገር ደህንነት ሚስጥር አጠባበቅ ሲባል የሚቆመው ተከላካይ ጠበቃ ከሠራዊቱ አባላት ብቻ እንዲሆን ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

## 39. ስለ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ደረጃዎች

በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የሚቋቋሙት ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ደረጃዎች ይኖራቸዋል፡-

1/ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት፤ እና

2/ ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት።

## 40. የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን

1/ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 284 እስከ አንቀፅ 337 በተደነገጉት ወታደራዊ ወንጀሎች ተጠያቂ በሚሆኑ ሰዎች፤

ለ) በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 539 እስከ አንቀፅ 544 መሰረት በሠራዊት አባላት መካከል በሚፈፀሙ የግድያና የአስገድዶ መድፈር፣ እንዲሁም በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 269 እስከ አንቀፅ 283 በተደነገጉት አለማቀፍ የሰብዓዊ  ወንጀሎች እና የእጅ እልፊትና የአካል ማጉደል ወንጀሎች፤

ሐ) ማንኛውም የሠራዊት አባል በአገር ውስጥ በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ሆኖ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ወንጀሎች፤

መ) በውጭ አገር ግዳጅ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ከተሰማራ የጦር ክፍል ጋር የዘመተ የሠራዊት አባል ወይም ሲቪሎች በሚፈፅሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች፤

ሠ) በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ከሠራዊቱ ጋር የዘመቱ ሲቪሎች፣ የመደበኛ ፖሊስ አባላትና ሚሊሻዎች በሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች፤

ረ) የጦር ምርኮኞች ከተማረኩ በኋላ በሚፈፅሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች፤

ሰ) ምልምል ወታደሮች ወደ ማሰልጠኛ ከገቡ በኋላ ወይም የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይል አባላት ወደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ከገቡ ወይም ከመደበኛ ሠራዊት ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ በሚፈጽሟቸው በወታደራዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎች፤

ሸ) በውጊያ የተማረኩ ሰዎች የጦር ምርኮ✹ች መሆን አለመሆና☯ዉን የመለየት ጉዳዮች።

2/ አንድ ተከሳሽ ከቀረበበት ክሶች መካከል ከፊሉ በወታደራዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር ከፊሉ ደግሞ በመደበኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ከሆነ ሁሉም ክሶች በወታደራዊ ፍርድ ቤት ተጠቃለው ይታያሉ፣

## 41. የይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሥልጣን

1/ ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት በቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያገኙ ጉዳዮችን በይግባኝ የማየት ስልጣን ይኖረዋል፣

2/ ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትን ውሣኔ የማፅናት፣ የማሻሻል ወይም የመሻር ስልጣን ይኖረዋል።

## 42. ስለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በወታደራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።

## 43. ስለወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞችና ብይኖች ተፈጻሚነት

ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ከዳኝነት ሥልጣናቸው ጋር በተያያዘ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞችና ብይኖች በማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ። ፍርድ ቤቶቹ እነዚህን ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞች ወይም ብይኖች የማይፈጽም ማንኛውንም ሰው ወይም አካል በሕግ መሠረት የመቅጣት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

## 44. ስለሞት ቅጣት አፈፃፀም

በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የተወሰነ የሞት ቅጣት በአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ካልፀና ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም። በይቅርታ ወይም በምህረት ያልተሻረ ወይም ያልተለወጠ መሆኑ አስቀድሞ ከመመርመሩና ከመታወቁ በፊት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 45. ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩባቸው የሥነ-ሥርዓት ህጎች

1/ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ እና እንዳስፈላጊነቱም የፍትሀብሔር ስነ ስርዓት ህግ እንዲሁም የማስረጃ ህጎች መሠረት በማድረግ ያስችላሉ፣

2/ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች መካከል በውሳኔ አሰጣጥ ልዩነት ሲኖር በድምፅ ብልጫ ይወሰናል።

## 46. ስለወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት፣ የሥራ ዘመንና ከዳኝነት ስለመነሣት

1/ በውትድርና አገልግሎት ላይ ያለና የህግ ዕውቀት ያለው መኮንን ወይም በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በዳኝነት በማገልገል ላይ ያለ ሲቪል በወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል፣

2/ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በመከላከያ ሚኒስትሩ ይሾማሉ፣

3/ የይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይሾማሉ፣

4/ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትና የይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፣

5/ ዳኞች ከሥራ የሚነሱት በህመም ምክንያት ተግባራቸውን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችሉም ተብሎ ሲወሰን ወይም በዲስፕሊን ጉድለት ወይም በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ነው፣

6/ ዳኞች ከሥራ የሚነሱት በሾማቸው አካል ይሆናል፣

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5) እና (6) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የሠራዊት አባል ዳኛ በልዩ ሁኔታ ለሌላ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሹመት ዘመኑ ባያበቃም ለሾመው አካል በማሳወቅ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ትዕዛዝ ከዳኝነት ሊነሣ ይችላል።

**47. <u>ስለችሎት አሰያየም</u>**

1/ እስከ ሶስት ዓመት በሚያስቀጣ ቀላል ወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳይ በአንድ ዳኛ ሊታይ ይችላል፤

2/ ከሶስት ዓመት ፅኑ እስራት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳይ ወይም የጦር ምርኮኞችን ህጋዊ አቋም የመለየት ጉዳይ የሚታየው ከሦስት ባላነሱ ዳኞች ይሆናል፤

3/ በይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚያስችሉ ዳኞች ብዛት ከሦስት ያላነሰ ሆኖ ሰብሳቢው ዳኛ ሲቪል ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ተግባራት የዳኞች ቁጥር ባይሟላም በአንድ ዳኛ ሊከናወኑ ይችላሉ፡-

ሀ) የክስን ህጋዊ ብቃት ማረጋገጥ፤

ለ) የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች በበቂ ምክንያት ባልቀረቡ ጊዜ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት፤

ሐ) ተከሳሽ ወይም ምስክር መጥሪያ ደርሶት ሳይቀርብ ቢቀር ተይዞ እንዲቀርብ ወይም ያልቀረበው መጥሪያ ሳይደርሰው ከሆነ ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት፤

መ) ጉዳዩ በተቀጠረበት ዕለት ያልተሰራ ከሆነ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠትን የሚመለከቱ ትዕዛዞች።

5/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ተግባራት የዳኞች ቁጥር ባይሟላም በሁለት ዳኞች ሊከናወኑ ይችላሉ፡-

ሀ) በክስ ላይ የቀረበን መቃወሚያ በመስማት ወይም የዋስትናን ጥያቄ በመስማት ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት፤

ለ) የይግባኝ አቤቱታ መስማት፤

ሐ) በሦስት ዳኞች የተሰጠን ፍርድ ለተከራካሪ ወገኖች መግለፅ።

6/ በቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ከሚሰየሙ ዳኞች መካከል ቢያንስ ሰብሳቢው ዳኛ በወንጀል ተጠርጥሮ ከተከሰሰው ሰው የበለጠ ወይም አቻ ማዕረግ ሊኖረው ይገባል፣

7/ በመከላከያ አቻ ማዕረግ ያልተገኘለት ሰው ተከሳሽ የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው ዳኛ በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይሰየማል።

## 48. ስለዳኞች ከችሎት መነሣት

1/ ዳኛው ከተከራካሪዎች ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ ወይም ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችለው ሌላ ምክንያት መኖሩን ሲያምን ወይም በማናቸውም ምክንያት እንዳያስችል ማመልከቻ ሲቀርብበትና ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ ከችሎት ይነሳል፤

2/ አንድ ወታደራዊ ዳኛ በሚመራው ክፍል አባል የሆነ ተከሣሽ ጉዳይ ሲቀርብ ወይም አባሉ ባይሆንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ጉዳዩን ቀድሞ ያወቀው እንደሆነ በችሎት አይሰየምም፣

3/ አንድን ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩ እንደታወቀ መሆን አለበት፤

4/ ከችሎት እንዲነሳ በማመልከቻ ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ የማመልከቻውን አግባብነት ከተቀበለው ከችሎቱ ይነሳል፤ ካልተቀበለው በሌሎች ዳኞች እንዲወሰን ማመልከቻውን ያስተላልፋል፤

5/ ከችሎት እንዲነሳ ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚያስችልበት ጊዜ ከሆነ ተቃውሞ የቀረበበት ዳኛ በሌለበት በሌሎች ዳኞች ውሣኔ ያገኛል።

## 49. ስለዳኝነት ነፃነት

1/ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶችና ዳኞች ከማንኛውም የመንግስት አካልም ሆነ ባለሥልጣን፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ከግል ድርጅቶች ወይም ከማንኛውም ሰው ተጽዕኖ ነፃ ሆነው ሥራዎቻቸውን ያከናውናሉ፤

2/ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶችና ዳኞች የስነ-ምግባር፣ የሥራ አፈፃፀም ብቃት፣ ተጠያቂነትና ነፃነትን የሚከታተል ከወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሁለት፣ ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሁለት እና ከአዛዦች አንድ አባል ያለበት የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ ይቋቋማል፤

3/ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ይቋቋማል፤

4/ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የሥነ-ምግባር ጉድለት ተፈፅሟል ተብሎ ጥቆማ ወይም አቤቱታ የቀረበበትን ዳኛ ጉዳይ አጣርቶ ውጤቱን ዳኛውን የመሾም ስልጣን ወዳለው አካል ያቀርባል፤

5/ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን የስራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ የመፍትሄ ሃሣብ ያቀርባል፤

6/ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥነ-ምግባር ኮሚቴ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚረዳው ዝርዝር የስራ መመሪያ ያዘጋጃል።

## 50. ስለ ፍትህ አካላት ተጠሪነት

በተቋሙ ውስጥ ነፃና ሚዛናዊ የፍትህ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ፦

1/ ወታደራዊ መርማሪ እና ወታደራዊ ዐቃቤ ህግ ተጠሪነታቸው ለጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ይሆናል።

2/ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እና ተከላካይ ጠበቃ ለመከላከያ ሚንስትሩ ተጠሪ ይሆናሉ።

## ክፍል ስድስት

## ሜዳይ፣ የምስክር ወረቀትና

## የተሸላሚዎች ልዩ መብቶች

### 51. ለመከላከያ ሠራዊት አባላት የሚሰጡ ሜዳዮችና የምስክር ወረቀቶች

1/ በመንግስት የሚሰጡ

ሀ) የጥቁር አንበሳ የላቀ ሜዳይ፤

ለ) የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ፤

2/ በሚኒስቴሩ የሚሰጡ

ሀ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

ለ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

ሐ) የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፤

መ) የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ፣

ሠ) የታማኝ ጀግና የብር ኮከብ ሜዳይ፣

ረ) የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ፤

ሰ) የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ፣

ሸ) የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ፣

3/ በኃይሎች፣ በዕዞችና ዋና መምሪያዎች የሚሰጡ

ሀ) የምርጥ አዛዥ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

ለ) የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

ሐ) የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

መ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

ሠ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

ረ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

ሰ) የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

ሸ) የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

ቀ) የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

በ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

ተ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

ቸ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፤

ኅ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አራተኛ ደረጃ፤

ነ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አምስተኛ ደረጃ፤

ኘ) የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ስድስተኛ ደረጃ

አ) የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ፤

ከ) የውጊያ ተሳትፎ የምስክር ወረቀት።

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) "ሀ" እና "ለ" ለተጠቀሱት ሜዳዮች በርዕሰ ብሄር የተፈረመ የምስክር ወረቀት ከሜዳዩ ጋር አብሮ ይሰጣል፣

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከ"ሀ" እስከ "ሰ" ለተጠቀሱት ሜዳዮች በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ የምስክር ወረቀት ከሜዳዩ ጋር አብሮ ይሰጣል፣

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) "ረ" ለተጠቀሰው ሜዳይ በመከላከያ ሚኒስትሩ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ከሜዳዩ ጋር አብሮ ይሰጣል፣

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከ"ሐ" እስከ "ቀ" የተጠቀሱት ሜዳዮች የውጊያ ድጋፍ ወይም የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ክፍሉ ሲያሚ በሜዳዩቹ ላይ ይፃፍባቸዋል፣ ሜዳዮቹ ለተሰጣቸው አባላት ወይም አሀዶችም በሰጪው አካል የተፈረመ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣

8/ የሜዳዮች፣ ሪባንና የምስክር ወረቀቶች መጠን፣ ቅርጽና ይዘት በደንብ ይወሰናል።

## 52. የጥቁር አንበሳ የላቀ ሜዳይ

1/ የጥቁር አንበሳ የላቀ ሜዳይ የሀገርን ህልውና እና ሉአላዊነት ከከባድ አደጋ ለመታደግ እጅግ ከፍተኛ አመራር የሰጠ፣ የሀገር አንድነትና ዳር ድንበርንና ህገመንግስታዊ ስርዓትን በታላቅ ጀግንነት ከከባድ አደጋ የታደገ፣ እጅግ የላቀ ጀብዱና ውለታ ለሀገር ለዋለ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ከፍተኛና የላቀ የጀግና ሽልማት ነው፣

2/ የጥቁር አንበሳ የላቀ ሜዳይ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ-ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በርዕሰ ብሔሩ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፤

ሐ) በፌደራሉ ርዕሰ ከተማ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል፤ በተጨማሪም መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምለት ይችላል፣

## 53. የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ

1/ የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ እጅግ የላቀ ጀግንነት በአውደ ውጊያ ለፈፀመ ወይም አመራር ለሰጠ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ከፍተኛ የጀግና ሽልማት ነው፡

2/ የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ-ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በርዕሰ ብሔሩ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፤

ሐ) በትውልድ ሥፍራው ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል።

3/ የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ ሁለት ጊዜ የተሸለመ ሰው በፌደራሉ ርዕሰ ከተማ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል፤ በተጨማሪም መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምለት ይችላል፣

4/ የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን በርዕሰ ብሔሩ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ) እና ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌዎች ለሠራዊት አሃድና ቡድንም ተፈጻሚ ይሆናሉ። ስለሆነም በትውልድ ሥፍራ ምትክ ጀግንነቱ የተፈጸመበት ሥፍራ ይሆናል።

## 54. <u>የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ</u>

1/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ እጅግ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው።

2/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ-ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል።

3/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ሁለት ጊዜ የተሸለመ ሰው በትውልድ ሥፍራው ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል፣

4/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ሦስት ጊዜ የተሸለመ ወይም የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃና የአድዋ ድል ሜዳይ የተሸለመ ሰው በፌደራሉ ርዕሰ ከተማ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ አደባባይ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መጠሪያ በስሙ ሊሰየምለት ይችላል፣

5/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎች ለሠራዊት አሃድና ቡድንም ተፈጻሚ ይሆናሉ። ስለሆነም በትውልድ ሥፍራ ምትክ ጀግንነቱ የተፈጸመበት ሥፍራ ይሆናል።

## 55. <u>የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ</u>

1/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ-ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

3/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## 56. የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ

1/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ በተሰለፈበት አውደ ውጊያ የዘወትር ወታደራዊ ግዳጅ አፈጻጸም ከሚጠይቀው በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈጸመ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

3/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ የተሸለመ ሰው በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት በተለይ በሚወሰንለት የክብር ሥፍራ ይቀመጣል፣

4/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ ለሆነ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## 57. የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ

1/ የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ ከአውደ ውጊያ ውጪ በተለይ ባልታሰበ ሁኔታ በጠላት ታፍኖ ያለ በየትኛውም ደረጃ ያለ ኢትዮጵያዊ ወታደራዊ አዛዥ የሀገሩን ምስጢር በመጠበቅም ሆነ በሌላ መንገድ ለሀገሩ ባበረከተው የላቀ ታማኝነት የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ የተሸለመ ሰው በአዋጁ መሰረት የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ ተሸላሚ የሆነ ሰው የሚያገኘውን ክብርና ልዩ መብት ያገኛል፣

## 58. የታማኝ ጀግና የብር ኮከብ ሜዳይ

1/ የታማኝ ጀግና የብር ኮከብ ሜዳይ ከአውደ ውጊያ ውጪ ለሀገሩ ባበረከተው የላቀ ታማኝነት ለኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ የተሸለመ ሰው በአዋጁ መሰረት የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ ተሸላሚ የሆነ ሰው የሚያገኘውን ክብርና ልዩ መብት ያገኛል፣

## 59. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ

1/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ በአእምሮ ሥራ ወይም በፈጠራ ወይም በማናቸውም መስክ ለመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮ መሳካት የላቀና ወደር የሌለው ውጤት ላስገኘ ሰው ወይም የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው፤

2/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በብሔራዊ በዓል አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣኖች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በሚኒስትሩ የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

3/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ ለተሸለመ የሠራዊት አሃድ ወይም ቡድን በሚኒስትሩ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

**60. <u>የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ</u>**

1/ የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ በኢትዮጵያ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን ከደርግ/የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ መንግስት ጋር ከ1967 እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ/ም ድረስ በትጥቅ ትግሉ ከ10 ዓመት ያላነሰ ተሳትፎ ላለው ታጋይ የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ የተሸለመ ሰው በጦ/ኃ/ጠ/ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

**61. <u>የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ</u>**

1/ የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ያለዘንባባ በኢትዮጵያ ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን ከደርግ/የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ መንግስ ጋር ከ1967 እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ/ም ድረስ በትጥቅ ትግሉ ከ10 ዓመት በታች ተሳትፎ ላለው ታጋይ የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የትግል ተሳትፎ ሜዳይ ባለዘንባባ የተሸለመ ሰው በጦ/ኃ/ጠ/ኤታማዦር ሹም የተፈረመ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል፣

**62.<u>የተሳትፎ ሜዳይ</u>**

ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወይም ከአፍሪካ ህብረት የሰላም ማስከበር ግዳጅ ውጪ የመከላከያ ሰራዊቱ ለሚሳተፍባቸው ልዩ ግዳጆች የተሳትፎ ሜዳይ ሚኒስቴሩ አዘጋጅቶ ሊሰጥ ይችላል

**63. <u>የምርጥ አዛዥ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤</u>**

1/ በዘመኑ ውስብስብ ወታደራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ራሱን በማብቃት ከዘመኑ ወታደራዊ እድገትና አስተሳሰብ ጋር ለመሄድ የሚያስችል አቅም የፈጠረ፣ በአዛዥነት ችሎታው በአሀዱ ከፍተኛ ከበሬታና ተቀባይነት ያለው፣ የውጊያ ዝግጁነቱንና የማድረግ አቅሙን በከፍተኛ ደረጃ የገነባ፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ጉዳት **እጅግ በላቀ ደረጃ** የፈፀመ ወይም መፈፀም የሚችል አመራር፣ ስታፍና ተዋጊ ኃይል ለገነባ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የተቋሙ ኃላፊዎች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

**64. <u>የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤</u>**

1/ በዘመኑ ውስብስብ ወታደራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ራሱን በማብቃት ከዘመኑ ወታደራዊ እድገትና አስተሳሰብ ጋር ለመሄድ የሚያስችል አቅም የፈጠረ፣ በአዛዥነት ችሎታው በአህዱ ከበሬታና ተቀባይነት ያለው፣ የውጊያ ዝግጁነቱንና የማድረግ አቅሙን በከፍተኛ ደረጃ የገነባ፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ጉዳት **በላቀ ደረጃ** የፈፀመ ወይም መፈፀም የሚችል አመራር፣ ስታፍና ተዋጊ ኃይል ለገነባ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የተቋሙ ኃላፊዎች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

## 65. <u>የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤</u>

1/ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ለሁኔታዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የውጊያ ዝግጁነትና የማድረግ አቅም በግሉም ይሁን በሚመራው አሀድ በከፍተኛ ደረጃ የገነባ፣ ጥሩ የአዛዥነት ችሎታ ያለው፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ጉዳት **በከፍተኛ ደረጃ** የፈፀመ ወይም መፈፀም የሚችል አመራር፣ ስታፍና ተዋጊ ኃይል ለገነባ የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት በተለይ በሚወሰንለት የክብር ሥፍራ ይቀመጣል፣

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

## 66. <u>ምርጥ ተዋጊ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤</u>

1/ ማንኛውንም ውስብስብና ፈታኝ ወታደራዊ ግዳጆችን ለመወጣት በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ክህሎት፣ በአካልና በስነ ልቦና እጅግ የላቀ የዝግጁነት ደረጃን ያረጋገጠ፣ ለየትኛውም አይነት ግዳጅ በአመራሩ ተመራጭ የሆነ፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ **እጅግ በላቀ** ደረጃ ለፈፀመ ወይም ሊፈፅም እንደሚችል በአመራሩና በአህዱ ለሚታመንበት የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የተቋሙ ኃላፊዎች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

መ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተቀመጠው መመዘኛ ጋር ተዛማጅ የሆነ ብቃት ላረጋገጠ አሀድም ሊሰጥ ይችላል፣

## 67. <u>ምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤</u>

1/ ማንኛውንም ውስብስብና ፈታኝ ወታደራዊ ግዳጆችን ለመወጣት በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ክህሎት፣ በአካልና በስነ ልቦና እጅግ የላቀ የዝግጁነት ደረጃን ያረጋገጠ፣ ለየትኛውም አይነት ግዳጅ በአመራሩ ተመራጭ የሆነ፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ **በላቀ** ደረጃ ለፈፀመ ወይም ሊፈፅም እንደሚችል በአመራሩና በአህዱ ለሚታመንበት የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት ለከፍተኛ የተቋሙ ኃላፊዎች በሚዘጋጀው ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

መ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተቀመጠው መመዘኛ ጋር ተዛማጅ የሆነ ብቃት ላረጋገጠ አህድም ሊሰጥ ይችላል፣

## 68. <u>ምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤</u>

1/ ማንኛውንም ውስብስብና ፈታኝ ወታደራዊ ግዳጆችን ለመወጣት በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ክህሎት፣ በአካልና በስነ ልቦና እጅግ የላቀ የዝግጁነት ደረጃን ያረጋገጠ፣ የተሰጠውን ግዳጅ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ከሚጠይቀው በመለስ **በከፍተኛ** ደረጃ ለፈፀመ ወይም ሊፈፅም እንደሚችል በአመራሩና በአህዱ ለሚታመንበት የሠራዊት አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ የተሸለመ ሰው፡-

ሀ) በተቋማዊ በዓላት አከባበር ስነ ስርዓት ወቅት በተለይ በሚወሰንለት የክብር ስፍራ ይቀመጣል፤

ለ) በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

መ) የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተቀመጠው መመዘኛ ጋር ተዛማጅ የሆነ ብቃት ላረጋገጠ አህድም ሊሰጥ ይችላል፣

## 69. <u>የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤</u>

1/ የዘመኑ ውስብስብ ወታደራዊ ተልዕኮዎች የሚጠይቁትን ዝግጁነትና የማድረግ ችሎታ መሰረት በማድረግ የሚደግፈውንና የሚያገለግለውን ሠራዊት ሙያዊ ግዴታው ከሚጠይቀው አፈፃፀም በላይ በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በስነልቦና ዝግጁ ያደረገ፣ በውጊያ ወቅት በማንኛውም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሠራዊቱ ግዳጁን በአስተማማኝ ደረጃ እንዲወጣ **እጅግ የላቀ የውጊያ** ድጋፍ ወይም የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ በቀጣይነት መስጠት ለቻለ የሠራዊት አባል ወይም አህድ የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የተሸለመ አባል ወይም አህድ በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

## 70. የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

1/ የዘመኑ ውስብስብ ወታደራዊ ተልዕኮዎች የሚጠይቁትን ዝግጁነትና የማድረግ ችሎታ መሰረት በማድረግ የሚደግፈውንና የሚያገለግለውን ሠራዊት ሙያዊ ግዴታው ከሚጠይቀው አፈፃፀም በላይ በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በሰነልቦና ዝግጁ ያደረገ፣ በውጊያ ወቅት በማንኛውም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሠራዊቱ ግዳጁን በአስተማማኝ ደረጃ እንዲወጣ የላቀ የውጊያ ድጋፍ ወይም የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ በቀጣይነት መስጠት ለቻለ የሠራዊት አባል ወይም አሀድ የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የተሸለመ አባል ወይም አሀድ በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

## 71. የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

1/ የዘመኑ ውስብስብ ወታደራዊ ተልዕኮዎች የሚጠይቁትን ዝግጁነትና የማድረግ ችሎታ መሰረት በማድረግ የሚደግፈውንና የሚያገለግለውን ሠራዊት ሙያዊ ግዴታው ከሚጠይቀው አፈፃፀም በላይ በሰላም ጊዜ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በሰነልቦና ዝግጁ ያደረገ፣ በውጊያ ወቅት በማንኛውም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሠራዊቱ ግዳጁን በአስተማማኝ ደረጃ እንዲወጣ ከፍተኛ የውጊያ ድጋፍ ወይም የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ በቀጣይነት መስጠት ለቻለ የሠራዊት አባል ወይም አሀድ የሚሰጥ ሽልማት ነው፣

2/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ የተሸለመ አባል ወይም አሀድ በኃይል፣ በዕዝ፣ ወይም በዋና መምሪያ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊ የተፈረመ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

## 72. ስለ ውትድርና አገልግሎት ሜዳይና ሪባን

በሥነ-ምግባርና በወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት የጉላ እንከን የሌለበት ማንኛውም የሠራዊት አባል እንደየአገልግሎት ዘመኑ የሚከተሉት የሜዳይና ሪባን ሽልማቶች ይሰጡታል፡-

1/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ከ40 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፤

2/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ከ35 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፤

3/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ ከ30 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፤

4/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አራተኛ ደረጃ ከ25 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፤

5/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ አምስተኛ ደረጃ ከ20 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፤

6/ የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ስድስተኛ ደረጃ ከ12 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ፣

7/ የውትድርና አገልግሎት ሪባን ለ7 ዓመት አገልግሎት።

## 73. የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ

የአውደ ውጊያ ቁስለኛ ሜዳይ በአውደ ውጊያ ተሰልፎ የመቁሰል አደጋ ለደረሰበት ሰው የሚሰጥ ሽልማት ነው።

## 74. <u>የሜዳይ ተሸላሚ የሚያገኘው ተጨማሪ ልዩ መብት</u>

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 (1) እና (2) እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ (3) ፊደል ተራ (ኘ) ሜዳይ ተሸላሚ

1/ በመንግስት ሆስፒታሎችና የሕክምና ተቋማት ውስጥ ነፃ ሕክምና ያገኛል፤

2/ በመንግስት የትምህርት ተቋማት ውስጥ ለመማር ቅድሚያ ያገኛል፤

3/ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶችና ተቋማት ውስጥ ችሎታው ለሥራ መደቡ ተስማሚ ሆኖ ሲገኝ የመቀጠር ቅድሚያ ይሰጠዋል።

## 75. <u>ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ ስለሞተ ሰው</u>

1/ ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ የሞተ ሰው አግባብ ያለው ሜዳይ በስሙ ይመዘገባል፣

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሜዳዩ ለታላቅ ልጁ ይሰጣል። ልጅ ከሌለው ለባለቤቱ፣ ባለቤት ከሌለው አግባብ ባለው የውርስ ሕግ መሠረት ለውርስ ባለመብቱ ይሰጣል።

## 76. <u>ከውጭ አገር ሜዳይ ወይም ሌላ ሽልማት ስለመቀበል</u>

ማንኛውም የመከላከያ ሠራዊት አባል ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ ከውጭ አገር ሜዳይ ወይም ሽልማት ሊቀበል አይችልም። ሆኖም ይህ ድንጋጌ የሠላም ማስከበር ሜዳይና ሽልማት ለመቀበል አይከለክልም።

## 77. <u>ሜዳይ፣ ሪባንና የምስክር ወረቀት መልሶ ስለመውሰድ</u>

ተሸላሚው፡-

1/ ሜዳዩ፣ ሪባኑ ወይም የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው በተሳሳተ ማስረጃ መሆኑ ሲታወቅ፤ ወይም

2/ በወንጀል ህጉ ከአንቀፅ 246 እስከ አንቀፅ 252 የተመለከቱትን ወንጀሎች መፈጸሙ በፍርድ ቤት ውሣኔ ሲረጋገጥ፤ የተሰጠው ሜዳይ፣ ሪባን ወይም የምስክር ወረቀት ይወሰድበታል። በሜዳዩ ወይም በሪባኑ ወይም በምስክር ወረቀቱ ምክንያት ሲጠበቅለት የነበረው መብትና ጥቅም አብሮ ይነሳል።

## 78. <u>የሜዳዮች ደረጃ ቅደም ተከተል</u>

የሜዳዮች ደረጃ ቅደም ተከተል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 በተመለከተው ዝርዝር ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል።

## 79. <u>የሜዳዮች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ</u>

በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ሜዳዮች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ በመመሪያ ይወሰናል።

## 80. <u>የገንዘብ ወይም የዓይነት ሽልማት የሚያስገኙ ሜዳዮች</u>

የገንዘብ ወይም የዓይነት ሽልማት የሚያስገኙ ሜዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1/ የጥቁር አንበሳ የላቀ ሜዳይ፣

2/ የአድዋ ድል ከፍተኛ ሜዳይ፤

3/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

4/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

5/ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፤

6/ የታማኝ ጀግና የወርቅ ኮከብ ሜዳይ፣

7/ የታማኝ ጀግና የብር ኮከብ ሜዳይ፣

8/ የላቀ የስራ ውጤት ሜዳይ፣

9/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

10/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

11/ የምርጥ አዛዥ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

12/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

13/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

14/ የምርጥ ተዋጊ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

15/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

16/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤

17/ የምርጥ ውጊያ ድጋፍ ወይም ውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ሜዳይ ሶስተኛ ደረጃ፤

**81. ስለሽልማቱ ዓይነትና ተጠቃሚዎች**

1/ ለግለሰብ ወይም ለቡድን የሚሰጠው የገንዘብ ሽልማት በህይወት ካለ ለራሱ፣ ከሞተም ለወራሾቹ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚከፈል ይሆናል፣

2/ ለሠራዊት አሃድ የሚሰጥ ሽልማት በአይነት ይሆናል፣ አጠቃቀሙን በተመለከተ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መመሪያ ይወሰናል፣

3/ ለእያንዳንዱ ሜዳይ የሚሰጠውን የገንዘብ ሽልማት መጠን ወይም ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች በተመለከተ በደንብ ይወሰናል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ አዋጅ የሜዳዮች ደረጃ አመዳደብ ብልጫ ያለው ሜዳይ ተሸላሚ የበለጠ ገንዘብ ተከፋይ ይሆናል፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**82. ስለ በጀት**

1/ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዓመታዊ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኘውን ገቢ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እያስፈቀደ ለመከላከያ አቅም ግንባታ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) የመከላከያ ተቋማት በሰላም ጊዜ የሚኖራቸውን የማምረትና አገልግሎት የመስጠት አቅም ለገቢ ማስገኛ ተግባር እንዲውል በማድረግ የሚገኘውን ገቢ፤

ለ) ለመከላከያ ጠቀሜታ የማያስፈልጉ ንብረቶችን በማስወገድ የሚገኘውን ገቢ፤

ሐ) በተቆጣጣሪ ባለሥልጣንነት ከሚመራቸው ድርጅቶች የሚገኘውን የትርፍ ድርሻ፤ እና

መ) ከሰላም ማስከበር ስምሪቶች የሚገኘውን ገቢ።

3/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን በጀትና ገቢዎች አስተዳደር በተመለከተ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ህጐች የተደነገጉትን ስርዓቶችና መመዘኛዎችን ተከትሎ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤ በውስጥ ኦዲተር፣ በዋናው ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ እንዲመረመር ያደርጋል።

## 83. ስለግዢና ንብረት አስተዳደር

1/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በፌደራል መንግሥት የግዢና ንብረት አስተዳደር ህግጋት መሠረት ግዢ በራሱ ይፈጽማል፣ ንብረቱን ያስተዳድራል፣ ያስወግዳል፣

2/ በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአገር ደህንነት አንፃር ወታደራዊ ሚስጥርነት ያላቸው ግዢዎችን የፌደራል መንግሥት የግዢ ህግጋትን ሳይከተል ሊፈፅም ይችላል፣

3/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ለአገር መከላከል ዓላማ የሚውሉ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ በነፃ ማስገባት ይችላል፣

4/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱትን ዕቃዎችና መሣሪያዎች በሚመለከት የጉምሩክ ዲክላራሲዮንና አባሪ ሰነዶችን እንዲያቀርብና ዕቃዎቹን ወይም መሣሪያዎቹን እንዲያስፈትሽ ወይም ሰነዶች እንዲያስመረምር አይገደድም።

## 84. የሂሳብ መዛግብት

1/ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በውስጥ ኦዲተሮች ይመረመራሉ፣

3/ በሚኒስትሩና በጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ አቅራቢነት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ለመከላከል ሲባል እጅግ ጥብቅ ሚስጥር ብሎ የሚሰይማቸውን የጦር መሳሪያና የውጊያ ቁሳቁስ የግዢ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች፣ ለመረጃ የወጡ የክፍያ ማስረጃዎች እንዳይገለፁ ሊያደርግ ይችላል።

## 85. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

2/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 እስከ 26 እንደተጠበቁ ሆኖ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሚኒስትሩንና የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፣

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**86. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

1/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን፣ ፍትህ ሚኒስቴርን፣ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽንንና የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደርን ጨምሮ ሁሉም የፌደራል የፍትህ ተቋማት በየስራ ዘርፋቸው የወታደራዊ ፍትህ አካላት ጋር የመተባበርና በአቅም ግንባታና በልዩ ልዩ የፍትህ ስርዓቱ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች የመደገፍና የማሳተፍ ኃላፊነት አለባቸው፣

2/ ሁሉም የፌደራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

**87. <u>የተሻረ ህግ</u>**

የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 እና 1232/2013 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

**88. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ …………..ቀን 2015 ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ መንግስት ፕሬዝዳንት